# ይድረስ ለውድ ወንድሜ “ለዲያቅቆን” ዳንኤል ክብረት

ውድ ወንድሜ የዛሬ ጽሁፌ መነሻ የሆነችኝን “ምናዝነው ስንት ሰው ሲሞት ነው?” ብለህ በሚያዚያ 20/2015 የጻፍካትን ጽሑፍ መልሰህ እንድታነባት ለመጋባዝ ነው።

በጽሑፍህ ላይ ሰባዊ ፍጡር ሁሉ የመጀመሪያ ስራው ማዘን ቀጥሎም ኀዘኑን በወጉ መግለጥ ነው ብለህ ነበር። አሁን  እንደ አንተ አባል መንግሥት ሰዎች ሲታረዱ፣ልጇ እያየች እናት ስትገደል፣ቤተክርሲያን አናስፈርስም ሲሉ ሰዎች ሲገደሉና ነዋዬ ቅዱሳንና ታቦት በኦሮሚያ ብልጽግና ኃይሎች ሲዘረፉ፣ በእምነታቸና በማንነታቸው ኢትዮጵያዊያን በገዛ ሀገራቸው ሲፈናቀሉ እንዲሁም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በጠላትነት ተፈርጀው ሲሞቱና ቁም ስቅላቸውን ሲያዩ በአንተ ዓይን ከሰባዊ ፍጡር በታች ስለሆኑ ወይስ ወኔህ ከድቶህ? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የእምነታችን ዋለታና ማገር የሆነውን ማኅበረ ቅዱሳንን ለመውቀስ 42 ገጽ ለመጻፍ የበረታው ክንድህ ዛሬ ለምን ዛለ? **በአህዛቡ ት.ህ.ነ.ግ** ዘመን ክርስቲያኖች በሊቢያ ሲሰዉ ከስንክሳሩ በመጥቅስ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን ፍጅት ሁሉ አዛምደህ ስታወሳ አሁን በዓይንህ **በአረመኔው አዴፓ ብልጽግና** ዘመን በክርስቲያኖች ላይና በቤተክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን ማአት በዓይነህ እያየህ ያለውን ሃቅ ለመናገርና ለመጻፍ ለምን አቃተህ? እባክህ ንገረኝ አሁን በምታምነው በዋቃፌና እምነትህ ይዝሃለሁ?

ወንድም ዳንኤል በኢትዮጵያ ላይ አዲስ ህግ ወጥቶ እንደሆነ ቁርጡን ንገረኝ ተበዳይ የሚከሰስበት በዳይ የሚወደስበት ምድር መሆኗን እያየህ ዝም ያልክ በፍርድ እየተከናወነ ስለሆነ ነው ወይስ ለሦስት ሥርዐት በባርነት ካገለገለችው ፕሬዝዳት ልምድ በማግኘትህ? እኛማ አማካሪ ስትባል ደስ ብሎን ነበር ለካስ ተመካሪ ኑረሃል። ተሾመ አሰግድ እኮ በዘፈኑ እንዲህ ብሎ ነበር
ፍቅር ያሸነፈው አቤት የሚልበት፣

መውደድ ያሸነፈው አቤት የሚልበት፣

ፍርድ ቤት ወይ ሸንጎ ቢኖር ምን አለበት፣

አይቆጨኝም ነበር ሺ ዓመት ብሚገት። በማለት አቀንቅኖ ነበር። እዚህ ዘመን ተበዳይ ሲከሰስና ሲታሰር ሲያይ ምን ይል ይሆን? ፍርድ ቤትና ሸንጎ በየቦታው ሞልቶ ነፍሰ ገዳይ በዳኞች አይዞህ ገና ብዙ ግዳይ ትጥላለህ ሲባል እየሰማን እያየን ወደ ላይ ከማንጋጠጥ በላይ የምናደርገው ጠፍቶን የሞታችንን ወረፋ እየጠበቅን እንገኛለን ። ህፃን ልጅ ሆኜ “ ፍርደ ገምድል ዳኛ” የሚል ተረት መጽሐፍ ነበር። ታድያ በዚያ የተረት መጽሐፍ ረጅሙ ሰው በሰራው ወንጀል አጭሩ ሲሰቀል ሲተረክልን ምን ያህል እናዝንና እንቆጨ እንደነበር ያውም ተረት መሆኑን ረስተን እውነት እያደረግን። በዚያ ጨቅላ አዕምሮአችን ዳኛውን ብናገኘው እንገለዋለን እያልን እንፎክር እንደነበረ ተረቱን የሰማነው ሁሉ እናስታውሳለን። በዛ ጨቅላ ዘመናችን ለትክክለኛ ፍትህ የነበረን ስሜት ዛሬ ግን አለ? ዛሬ ግን ፍርደ ገምድልነቱ ከተረት መጽሐፍ ወጥቶ በነ አኖሌ አባትና በቄሮዎች ሲፈጸም እያየን ለምደነው በሰላም እንተኛልን። አዎይ ጊዜ?

ወንድም ዳንኤል የዛሬ ሁለት ዓመት ይመስለኛል ሜልበርን ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል መጥተህ በነበረበት ሰዓት ስታስተምር **“ዕውቅት የሌለው እምነት ድንበሩ ሞኝነት ሲሆን፤ እምነት የሌለበት ዕውቀት ደግሞ ድንበሩ ትዕቢት ነው።”** ብለህ እንደ ነበረ ማስታወሻዬ ላይ አግኝቸዋለሁ። ታዲያ አሁን አንተን በየተኛው እንመድብህ? እውቀት በማጣቱ ወይስ እምነት በማጣቱ? ሁሉቱም እንደሆኑ አሁን ግልጽ ሆኗል። እውቅት በማጥቱ ባለፈው በርዕዬት ድምጽ አቻምየለህ በማስረጃ አስቀምጦታል። ከዚህ በፊት ፕሮፌሰር መስፍን ጠቁመዉት ነበር። እምነት በማጣት የሚለው ደግሞ አሰላለፍህን ከአረመኔዎች ጋር ማድረግህ ግልጽ ማስረጃ ነው። እኔም ደግሞ **“በመላለስ ላይ ብቻ የተመሰረተ እምነት መነሻው ትችት፤ መድረሻው ትምክህት።”** መሆኑን አሰላለፍህና ጊዜ ይህን አሳይቶናል።

ወንድም ዳንኤል ስለ እንደ አንተ ያሉትን ክርስቲያን ነን ባዮች አቡነ ሺኖዳ ሲያስተምሩ **“ብዙዎች እግዚአብሔርን ሳያገለግሉ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች ይሆናሉ።” ሲሉ** ሼክስፒር ደግሞ **“ ለቤተክርስቲያን በጣም ቅርብ የሆኑ፤ ለእግዚአብሔር ግን በጣም የራቁ ብዙ ሰዎች አሉ።”** ብሏል። አንድ የምለው መፈክር ቢጤ አለኝ “ የገዛ ታሪኩን የሚክድና የሚያጥላላ ትውልድ ከእንግዴ ልጅ እኩል ነው!!!” ያውም ከዋናው የእንግዴ ልጅ የአኖሌ ሐውልት ባለቤትና አስገንቢ( አብይ) ፍጽም ቀጣፊ ከሆነ ግለሰብ ጎን መሰለፍህ ራስህን ብቻ ሳይሆን ታላቂቱ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ማሰደብህናን እኛንም ተከታዮቿን በትልቁ ያሸማቀቀና ያዋረደ እንደሆነ ልታውቀው ይገባል። ሜልበርንም ስትመጣ እንደ አባ ወልደ ጊዮርጊስ ያሉትን የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ዜግነታቸውነን ሲለውጡ መገሰጽ ሲገባህ በዝምታ ወደ መጣህበት እንደምትመለስ አውቃለሁ። መፃፈ መነኮሳት የሴት ድምጽ የማይሰሙበት ይኑሩ ፣ምንኩሱና መሞት ነው ዓለምን መተው ነው እንደሚል ለሚያውቅ ሰው ዓለማዊ ሲሆኑ ማየት እጅግ ያማል። እኔም በዚህ በመከፋቴ በግልጽ ነግሬ ቤተክርስቲያን መመላለሴን ትቼ እቤቴ ለመጸለይ ተገድጃለሁ። “ ዓሣ ከባህሩ ከውጣ፤መነኩሴ ካባህቱ ከለቀቀ ሁለቱም የሞቱ ናቸው።” አቡነ ሺኖዳ፤ ከቤተክርስቲያኗ ሥራዓት ከተውጣ ይህ እኮ ተሃድሶነት ነው። ይህ ለነበጋሻው ብቻ ነው የሚሰራው? ይህ ምን ችግር አለው? ማለት አንዳርጋቸው ጽጌን ያስታውሰኛል። ተስፋዬ ገ/አብ የደራሲው ማስታውሻን አብረህ የምታረቅ ለምንድን ነው የቡርቃ ዝምታ ጸሐፊ መሆኑን ዘነጋህ እንዴ ስለው ቃል በቃል ያለኝ የቡርቃ ዝምታ ምን ችግር አለው ነበር!!! ሜልበርን መድሐኒያዓለም ቤተክርስቲያን ሁለት መነኮሳት አፍርሰው ትዳር መመስረታቸውንና ልጆች መውለዳቸው የአደባባይ ሚስጥር እንደሆነ ይታወቃል። ዳንኤል ክብረት ግን መነኮሳት ዜግነታቸውን እንደለወጡ እያወቀ ምን ቸገረኝ ብሎ ማለፉ የቆመው ለገንዘብ እንጂ ለእምነቱ እንዳልሆነ በግልጽ አሳይቶናል። ዶ/ር አባ ኃይለማሪያም መለሰን ኢኩሚኒዝም በሚል የዓለም ሐይማኖቶችን አንድ በሚያደርግ ማህበር አባል

በመሆን ከዶ/ር ኦላቪ ፍይክሴ( Dr.Olav Fykse Tyeit) በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ውስጥ በአንዲት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በግልጽ የቅባ ቅዱስ መቀባባት የፈጸሙ መነኩሴ እንደሆኑ እየታወቀ በሜልበርን ቅዱስ ሚካኤል ቤተክሪስትያን ውስጥ መቀደሳቸውን በመጣህ ጊዜ ተነግሮህ የነበረ ቢሆንም በዝምታ ስታልፈው በደመነፍስ የሚንቀሳቀሰው መዕምን ከቁብ አልቆጠረውም። በዚህም እምነት አቡነ ጳውሎስና አቡነ ማቲያስ አባል መሆናቸው ግልጽ ነው። የአቡነ ጳውሎስ፣የአቡነ ማትያስን፣ የአቡነ ሄኖክንና የአባ ኃይለማሪያምን እን ለማየት የፈለግ "አዲሱ የዓለም መንግሥት ሐይማኖቶች" ከክፍል1-3 በ Aesop Ethiopia youtube ማየት በቂ ምስክር ነው። ጨርሻለሁ።

## አንተነህ ጌትነት ሙላቱ( የሶማው) ከባዕድ ሀገር አውስትራሊያ ሜልበርን